ቅጽ 4 ቁጥር 2

ዜና መጽሔት

# ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት
# Tourism training institute

## ከሆቴልና ቱሪዝም ማሰልጠኛ ማዕከል ወደ ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት

አንጋፋው የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ማዕከል በአዲስ አደረጃጀት የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት መባሉ ተቋሙ ለረዥም ጊዜ ሲጠየቅ የነበረውን ጥያቄ የመለሰ ነው ሲሉ የተቋሙ ዋና ዳይሬክተር ወ/ሮ አስቴር ዳዊት ገለጹ፡፡

ወደ ገጽ 6 የዞረ



## የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ተጠሪ ሆኖ በአዲስ መልክ ከተዋቀረው የሥራና ክህሎት





በዕለቱ ከሁሉም ተጠሪ ተቋማት ጋር በአስተዳደር ዘርፍ ያሉ ሠራተኞች ጋር ትውውቅ ያደረጉት የሥራና ክህሎት ሚኒስትር ክብርት ሙፈሪያት ካሚል የእንኳን ደህና መጣችሁና የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ እንደ ሀገር የተሰጠውን ተልዕኮና የሚያስፈጽመውን ዓላማ አስተዋውቀዋል።

በዚህ አዲስ አደረጃጀት ውስጥ አስር ያህል ተቋማት በአዲስ የተደራጅተዋል።

ተቋማችን በሆስፒታሊቲው ኢንደስትሪ ሥልጠና በመሥጠት የራሱን ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል።በተለይ ደግሞ በዘርፉ ሙያዊ ክህሎት አዳብሮ መያዝ የሚችል ፤ የነበረውንም የካበተ ልምድ በመጠቀም ለወጣቶች ብቃት ያለው ሥልጠና መሥጠት የሚያስችል አበርክቶ እንደሚኖረው ታምኖበታል።

በኢንስቲትዩቶች ያሉ መምህራንና አሰልጣኞች ጋር ቀጣይ የግንኙነት ጊዜ እንደሚኖር ክብርት ሚኒስትር ሙፈሪያት ካሚል ገልጸዋል።

በኮምኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት የተዘጋጄ

# ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት
# Tourism training institute

## ለቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት መምህራን የማነቃቂያ ስልጠና ተሰጠ




ቱ.ማ.ኢ.ጥቅምት 19/2014 ዓ.ም በሀገራችን የተጀመረውን አዲስ ምዕራፍ ወደ ተቋማችን ለማምጣት በቅድሚያ መምህራን የማነቃቂያ ስልጠና መውሰድ አስፈላጊ መሆኑን የተቋሙ ዋና ዳይሬክተር ወ/ሮ አስቴር ዳዊት ተናግረዋል።

ይህ ስልጠና ከሌላው ጊዜ ለየት የሚያደርገው ስልጠናውን የኢንስቲዩቱ ቦርድ ሰብሳቢ ፕሮፌሰር አፈወርቅ ካሱ ተሞክሯቸውን በተግባር እያየን ከትንሽ ገጠር ከተማ በመነሳት የኢትዮጵያ ፕሮፌሰር እና በተለያዩ ዓለም ሀገራት በሥራቸው ተሸላሚ መሆናቸው ነው በመጠቆም መምህራን ስልጠናውን በንቃት እንዲትከታተሉ አሳስበዋል።

ፕሮፈሰር አፈወርቅ ካሱ አዲሱን ዓመት ትምህርት ሰጀመር በመነቃቃት በአዲስ ምዕራፍ በአዲስ መንፈስ ከሰልጣኞቻቸው ጋር እንዲገናኙ በማሰብና ከህይወት ልምዳቸው በማስተማር እናንተም ትችላችሁ በሚል መሪ ቃል ስልጠና ሰጥተዋል። በስልጠናው የተነሱ ዋና ሀሳቦች ከዳውሮ እስከ ኮሎራዶ ጉዞዋቸውን በውስጡ ያሳለፉትን ተሞክሮ በመጥቀስ ሰፊ ስልጠና ሰጥተዋል። በተጨማሪም በትምህርትና ስልጠና እንዲሁም በምርምር ስራዎችም እንዴት መለወጥ እንዳለባቸውም ለመምህራኑ ተገጿል።

ኢትዮጵያ ከሌሎች ሀገራት በኢኮኖሚ ልቃ እንዲትታይ ትልቁ የእናንተ ግኝት እና ስራ መሆኑን ተረድታችሁ እውቀትን በመፈለግ ስራ ማድረግ እንደሚጠበቅባቸው በመግለጽ' እኔ ከትንሽ ገጠር ከተማ ወጥቼ እዚህ ከደረስኩ እናንተ ከዚህ በላይ መስራት ትችላላችሁ' ብለዋል።

'ተቋማችሁ 53 ዓመታት በሆቴልና በቱሪዝም ዘርፍ በርካታ ባለሙያዎችን አፍርቷል። ስለዚህ እናንተ የዚህ ዘርፍ እንቁዎች ናችሁ።' ኢትዮጵያ አፍሪካዊት የብልጽግና ተምሳሌት ለማድረግ ሰው የሆነ ሁሉ ጥረት ማድረግ እንዳለበት በመግለጽ እናንተም በራሳችሁ ዘርፍ ይህን ማሳካት እንደሚቻል ተናግረዋል።

መምህራን በስልጠናው እንደተደሰቱና በንግግር ብቻ ሳይሆን በተግባር ያሳዩ መሆናቸውን በማድነቅ ለቀጣይ ሥራቸው ብዙ ትምህርት እንዳገኙበት ተናግረዋል።

የፕሮፌሰር ልምድ ለሌሎች በተለያየ ዘርፍ ለሚገኙ ባለሙያዎችም በጣም አስፈላጊ መሆኑንም የጠቆሙት ተሳታፊ መምህራን ይህ ስልጠና ለብዙ ኢትዮጵያዊ ስለሚያስፈልግ ቢዳረስ በማለት አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።





# ለሰልጣኞች የማነቃቂያ ስልጠና በተቋሙ መምህራን

ቱ. ማ .ኢ .ጥቅምት 25/2014 ዓ.ም

ስልጠናውን በንግግር የከፈቱት የተቋሙ ዋና ዳይሬክተር ወ/ሮ አስቴር ዳዊት ሰልጣኞች ከመደበኛ ትምህርታቸው በተጨማሪ በተለያዩ ክበባት በመሳተፍ ከመጡበት የተለያየ ይዘውት የመጡትን ልምድ ለሌሎች ለማካፍል ምቹ ሁኔታ የሚፈጥር መሆኑን በመጠቆም ሥልጠናው በጥሩ ሥነምግባር የታነፃችሁ ሆናችሁ የተሻለ የትምህርት ተሳትፎ እንዲኖራችሁ የሚያደርግ ስለሆነ በአግባቡ እንድት ከታተሉ በማለት መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

የመጀመሪያውን ስልጠና የሰጡት መምህር ታረቀኝ መኮንን የክበባት እንቅስቃሴ በክፍል ውስጥ ከሚሰጥ ትምህርት በተጨማሪ እራስን ለማብቃትና ለተግባቦት እንደሚጠቅም ሰፊ ማብራሪያ ሰጥተዋል። መምህር ሞኮንን ጋሻው በበኩላቸው ሰልጣኞች በትምህርታቸውም ሆነ በኑራቸው በራስ መተማመን እንዲያዳብሩና ሁልጊዜም የህይወት መርሆዋቸው እችላለሁ እንዲሉ የሚያደርግ የማነቃቂያ ስልጠና ሰጥተዋል።



በተጨማሪም የተቋሙ ስነ-ምግባርና ጸረ-ሙስና ዳይሬክቶሬት አቶ ታምራት ተፈራ ለሰልጣኞች የተቋሙን ስነምግባር ደንብን፣ ከሰልጣኞች የሚጠበቀው መብትና ግዴታቸውንም ጭምር በስፋት በማንሳት ስልጠና ሰጥተዋል።።።

በመጨረሻም የተማሪዎች ፕሬዝዳንት በመምረጥና በተለያዩ ክበባት ለተደራጁት ተማሪዎች ሰብሳቢዎችን በመምረጥ ስልጠናው ተጠናቋል ።









**የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት በአቅራቢያ ለሚገኙት ትምህርት ቤቶች የወንበር ድጋፍ አደረገ።**

ቱ.ማ.ኢ ጥቅምት/2014 ዓ.ም

የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት በአቅራቢያ ለሚገኙት የአንደኛ ደረጃና አጸደ ህጻናት ትምህርት ቤቶች የወንበር ድጋፍ አደረጓል። ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩቱ ለሽመልስ ሀብቴ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤትና ለወንድማማቾች አጸደ ህጻናትና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ሰማኒያ ሺህ ብር ግምታዊ ዋጋ ያለው 250 የሚሆኑ ወንበሮችን አበርክቷል።



## የበጎ አድራጎት ሥራዎች በሰልጣኝ ተማሪዎች

ሰልጣኞችን በማስተባበር የበጎ አድራጎት ሥራዎች ለማከናወን ፕሮግራም መያዛቸውን የተማሪዎች ፕሬዝዳንት ተማሪ ዓለም ፀሀይ ጥጋቡ ተናገረች። ሰልጣኞችን በማስተባበር አሁን ካለው ከሀገራችን ወቅታዊ ሁኔታ አንጻር የበጎ አድራጎት ክበብ መጠናከር እንዳለበትና በተለያዩ አካባቢዎች ለተፈናቀሉ ወገኖች እንዲሁም ለመከላከያ ሠራዊታችን ድጋፍ እንደሚያሰባስቡ ተናግራ ለዚህ በጎ አድራጎት ሥራ የተቋሙ ማህበረሰብ ሙሉ ድጋፍ እንዲያደርግላቸው ጠይቀዋል። ስለሆነም ሀሙስ ህዳር 16/2014 ዓ.ም በገነት ሆቴልና በማሰልጠኛ ኢንስቲትዩቱ ትብብር የተቋሙ ሰልጣኞች በዋናነት መምህራንና ሠራተኞች የሚሳተፉበት ፕሮግራም ተዘጋጅቷል።

- የበጎ አድራጎት ሥራዎች፤
- የጽዳት ዘመቻ፤
- የደም ልገሳ ፤
- የደረቅ ምግብ ዝግጅት፤
- የአልባሳትና ቁሳቁስ ማሰባሰብ ዝግጅቶች የሚከናወኑ ይሆናል።

ድል ለመከላከያ ሰራዊታችን!!!

ኢትዮጵያ ታሸንፋለች



## The Institute renewed the partnership agreement

The Institute renewed the partnership agreement with French Embassy.

This agreement was signed before two years ago with French embay and Alliance Ethio France.

Within these two years the Embassy gives Scholarship for our French instructors, supportive materials for French departments.

Today's agreement was signed by the representative of our General Director Mr Abraham Legesse Academic and research dean, and Mrs Sophie Moal Head of Cooperation, Embassy of France.



# ደጀንነት በተግባር!!

ለመከላከያ ሰራዊታችን ያለንን ደጀንነትና በጦርነቱ ሳቢያ ከቤት ንብረታቸው ለተፈናቀሉ ወገኖቻችን አጋርነታችንን የምናሳይበት ፣ ብርታትና ጉልበት ለመሆን ያለንን ድጋፍ በተግባር ለመግለጽ ኢንስቲትዩታችን ከገነት ሆቴል ጋር በመተባበር ለሶስተኛ ጊዜ የገንዘብ፣ የቁሳቁስ፣ ደም ልገሳ፣ የደረቅ ስንቅ ዝግጅት እና የአልባሳት ድጋፍ አድርጓል።

3ኛው ዙር ህዳር 16/2014 ዓ.ም የተደረገው ድጋፍ በዓይነቱና በስፋቱ ለየት ያለ ሲሆን ጥቅል ዝግጅቱ የሚከተሉትን ፕሮግራሞችን ያካተተ ነበር።

ከማለዳው አንድ ሰዓት ጀምሮ በኢንስቲትዩቱ የሜክሲኮና ገነት ካምፓሶች የጽዳት ፕሮግራም የተካሄደ ሲሆን ይህም በተቋሙ ሰራተኞችና ተማሪዎች ትብብር የተካሄደ ነው።

በጽዳት ዘመቻው በተለይ በሜክሲኮ ካምፓስ ለረጅም ጊዜ አገልግሎት ሳይሰጡ የነበሩ ክፍሎችና ቢሮዎች ጭምር ጽዳት ተደርጎ ላቸው ለአገልግሎት ዝግጁ እንዲሆኑ ተደርጓል። ጽዳቱ በዋነኝነት በተማሪዎች ተነሳሽነት ኅዳር 12 "ኅዳር ሲታጠን" ከሚል ታሪካዊ ሂደት ጋር ተዛምዶ የተከናወነ ነው።

የአልባሳት ድጋፍ

የአልባሳት ማሰባሰብ ስራው እንዲሁ ቀድሞ ለሰራተኛውና ለተማሪዎች በተደረገ ቅስቀሳ

በዕለቱም ለመረከብ በተዘጋጁ ኮሚቴዎች አማካኝነት 50 ማዳበሪያ አልባሳት በዓይነት በዓይነታቸው ተሰብስበው ለተፈናቃይ ወገኞቻችን ለማድረስ ዝግጁ ተደርገዋል።

የደም ልገሳ ፕሮግራም

የደም ልገሳ ፕሮግራም ይህም ለሶስተኛ ዙር የተካሄደ ሲሆን በዚህኛው ዘር የነበረው ተሳትፎ በጣም ከፍተኛ ነበር ከቀይ መስቀል የደም ባንክ ተወክለው የመጡ ባለሙያዎችም በተሳትፏችን በጣም ተደስተው ምስጋናቸውን አቅርበዋል። በዚህ ፕሮግራም 85 የተቋሙ ተማሪዎችና ሰራተኞች ደም ለግሰዋል።












**የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ጥቅምት 24/13 ዓ.ም በመከላከያ ሰራዊታችን ላይ የተፈጸመውን አሳዛኝ ግፍ በዚህ መልኩ ተሰባስበው አስበዋል።**



ከገጽ 1 የዞረ

ተቋሙ ከተቋቋመበት ከ1961 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 2002 ዓ.ም ድረስ የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ተብሎ ስልጠና ሲሰጥ የቆየው ይህ ተቋም ከ2002 ዓ.ም በኋላ የደንብ ማሻሻያ ተደርጎለት ከኢንስቲትዩት ወደ ማዕከል ዝቅ ብሎ ላለፉት አስራ አንድ ዓመታት በቴክኒክና ሙያ ማዕቀፍ እስከ ደረጃ አምስት በሆቴልና በቱሪዝም ዘርፍ ሥልጠና ሲሰጥ መቆየቱ ይታወሳል።

ነገር ግን ይህ ደንብ ተቋሙ ከሚሰጣቸው ስልጠናዎች እና ለዘርፉ ካለው አንጋንፋነት ጋር ሥራውን አሳድጎ ለመሄድ አመቺ ባለመሆኑ በዘርፉ ባለሙያዎችና ተመድበው በሚመጡ የስራ ኃላፊዎች በየጊዜው የደንቡ ይሻሻልልን ጥያቄ ዛሬ ላይ ምላሽ ማግኘቱ ለተቋሙ ማህበረሰብም ሆነ ለዘርፉ ባለሙያዎች ትልቅ ደስታ እንደሆነ ወ/ሮ አስቴር ዳዊት ተናግረዋል።

ተቋሙ ከተጠሪነት አንፃር ሲታይ ላለፉት 53 ዓመታት በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር፣ በወቅቱ ከነበረ የኢትዮጵያ ቱሪዝምና ኮሚሽን ተጠሪ ሆኖ የቀጠለ ነበር። ሆኖም በአሁኑ አደረጃጀት በሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ውስጥ የገባበት ዋና ዓላማ በሀገራችን የሚታየውን የሥራ አጥ ቁጥር ለመቀነስ በተለያዩ የአጫጭርና የረጅም ጊዜ ስልጠናዎችን በመስጠት ሥራን ከሰራተኛ ጋር ለማገናኘት እንደሆነ ዋና ዳይሬክተሯ ገልጸዋል።

ቱሪዝም በባህሪው ከፍተኛ ቁጥር ያላቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች ወደስራ ማሰማራት የሚያስችል ትልቅ የኢኮኖሚ ዘርፍ በመሆኑ አገራችን ካላት ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ሀብቶች፤ ባህላዊና ታሪካዊ ቅርሶችን በመጠቀም ዘርፉን ለማልማትና ወጣቱም የዚህ ተጠቃሚ እንዲሆን የማሰልጠኛ ኢንስቲትዩቱ ያለው ድርሻ ከፍተኛ መሆኑን ጠቁመዋል።

ኢንስቲትዩቱ አሁን ባለው አደረጃጀትም ከዚህ ቀደም የሚሰጣቸውን የስልጠና የምርምርና የማማከር አገልግሎት በሰፊው ይሰጣል። ተቋሙ ብዙ ልምድ ባላቸው መምህራን የታገዘ እና 25 ያህል ቤተሙከራዎች እንዲሁም ገነት ሆቴልን ጨምሮ ልምድ የሚገኝበት ተቋም በመሆኑ ሌሎች በቱሪዝምና ሆቴል ስልጠና ለሚሰጡ ተቋማትም ጠቀሜታው የጎላ ነው ብለዋል።

ከዚህ በተጨማሪ ከተለያዩ ተቋማት በጋራ ለመስራት ይደረግ የነበረውን እንግልት በመቀነስ ተመሳሳይ ተቋማት ጋር አብሮ በአንድ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ሥር መካተቱ ለተቋሙ የተሻለ እንደሆነ ዋና ዳሬክተሯ ገልጸዋል።

ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር እና ቱሪዝም ሚኒስቴር በየራሳቸው በሚኒስቴር ደረጃ መውጣታቸው ለዘርፉ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳለው ገልጸው ከኛ ተቋም ጋር ደግሞ አብሮ ለመስራት የሚያስችሉ ስራዎች እንዳሉን እና የአስር ዓመት ዕቅዳችንም ሆነ በርካታ ስራዎች በጋራ ስምምነት በመፈራረም አብረን የምንሰራው ሥራ እንደሚኖር መገንዘብ አለብን ብለዋል። ተቋሙ ከዚህ በፊት የነበረውን ስያሜ መቀየርም ግርታ ሊፈጥርብን አይገባም።